ሕገ መንግሥቱ ለአብዛኛዎቹ ሠራተኞች በጋራ የመደራደርን መብት ከመስጠቱም በላይ፣ ሠራተኞች ይህንን መብታቸውን በነጻነት እንዲጠቀሙበት መንግሥትም በግብር ፈቅዷል። በአሠሪና ሠራተኞች ላይ ጥናት ያካሄዱ ሙያተኞች እንደገመቱት በማሕበር ከተደራጁት ሠራተኞች መካከል 90% የሚሆኑት ከአሠሪዎቻቸው ጋር የሕብረት ስምምነት ፈርመዋል። የደመወዝ ድርድር በፋብሪካ ደረጃ ተካሂዷል። የአሠሪና ሠራተኛ ደንቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ በኢንዱስትሪው ዘርፍ በሚሠሩ ሠራተኞች የተወሰኑ ጥረቶች ተደርገዋል። ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች የሚመረቱበት የተለዩ ቀጠናዎች የሉም።

ሠራተኞች ከሥራ ሲባረሩ በምን መልኩ ጥቅማቸውን ማስከበር እንደሚገባቸው፣ በርካታ የሠራተኛ ማኅበራት በአንድ የሥራ አካባቢ ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ፣ እና "አስፈላጊ አገልግሎቶች" ተብለው የተጠቀሱ አገልግሎት ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ መብትን የሚገድበው ዋናው የሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42 በኅዳር 1995 በፓርላማው ማሻሻያ ተደርጐበታል።

በሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42 ሠራተኞች ጥቅማቸውን ለማስከበር የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ እንደሚችሉ በግልጽ ቢደነገግም፣ የሥራ ማቆም አድማ ከማድረግ በፊት ቢያንስ የ130 ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ያሉ ገደቦችን እንደ ሚጥለው ዓይነት ዝርዝር አንቀጾች ስለአሉት፣ ሕጋዊ የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ ዕድልን አስቸጋሪ ያደርገዋል። ከ1985 ወዲህ አንድም ሕጋዊ የሥራ ማቆም አድማ አልተካሄደም። ቅር የተሰኙ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ከማድረጋቸው በፊት ረጅም ጊዜን የሚፈጅ የአለመግባባት መፍቺያ ሒደትን ማለፍ የሚጠይቅ ድርድር ማድረግ እንዳለባቸው ሕጉ ይጠይቃል። ይህ ሂደት በሩን ቆልፎ ሠራተኞቹ ወደ ሥራ ቦታቸው እንዳይገቡ ያደረገ አንድ አሠሪን መብት ጭምር ያካትታል። የሥራ ማቆም አድማ በሚመለከታቸው አብላጫ ሠራተኞች የተደገፈ መሆን ይኖርበታል።

ከላይ የተገለጹትን ሳያሟሉም ቢሆን፣ የተወሰኑ ቀላል እርምጃዎች እስከወሰዱ ድረስ ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ መብታቸውን ሊያስከብሩ ይችላሉ። ከሠራተኞቹ የሚጠበቀው ቢያንስ የ10 ቀን ማስጠንቀቂያ ለአሠሪያቸውና ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማቅረብ፣ በድርድር ለመፍታት ተገቢውን ጥረት ማድረግ እና ጉዳዩ በፍ/ቤት ወይም በሠራተኛ ግንኙነት ቦርድ በመታየት ላይ ከሆነ የ30 ቀናት ማስጠንቀቂያ መስጠት ነው።

ወሳኝ አገልግሎቶች የሚሰጡ ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ የአየር መጓጓዣ እና የምድር ባቡር፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅራቢዎች፣ አውቶቡስ የሚያንቀሳቅሱ፣ የነዳጅ ማደያ ጣቢያ ሠራተኞች፣ የሆስፒታልና የመድኃኒት ቤት ሠራተኞች፣ የባንክ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የፖስታና ቴሌካሙኒኬሽን፣ የከተማ ጽዳት ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ ሕጉ አይፈቅድም።

የዓለም የሠራተኛ ድርጅት (አሠድ) እንደገለጸው፣ የሠራተኛ አዋጁ ውስብስብነትና ለሕግ ተርጓሚው በተመደበው ገንዘብና የሰው ኃይል ውስንነት የተነሳ የአሠሪና ሠራተኛ አለመግባባት የፍርድ ሒደቶች ለወራትና ለዓመታት ይጓተታሉ።

የሥራ ማቆም አድማ ባደረጉ ሠራተኞች ላይ ቅጣት መጣል እንደሌለበት በሕግ ቢደነገግም፣ መንግሥት ይህንን ጥበቃ ተግባራዊ ስለማድረጉ ሙሉ እምነት እንደሌላቸው የማኅበር መሪዎች ተናግረዋል። በማኅበራት መሪዎች እምነት ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግርና የተጓተተ የአቤቱታ ሥርዓት በመኖሩ ምክንያት፣ የተወሰኑ ሠራተኞች በሥራ ማቆም አድማና በሌሎች የሠራተኛው እርምጃዎች ላይ ለመካፈል አይደፍሩም፤ ይፈራሉ።

ሐ/ በኃይል አስገድዶ ወይም በግዴታ ማሠራት ስለመከልከሉ

ሕጻናትን ጭምር በኃይል አስገድዶ ወይም በግዴታ ማሠራት በሕግ የተከለከለ ቢሆንም፣ እነዚህ ድርጊቶች ስለመኖራቸው ዘገባዎች ነበሩ (ክፍል 5 እና 6 መን ይመልከቱ)። በኃይል አስገድዶ ማሠራት በፍ/ቤት ትዕዛዝ በቅጣት መልክ ሊሰጥ ይችላል።

መ/ ሕጻናትን ማሠራት ስለመከልከሉና ስለቅጥር ዝቅተኛ ክፍያ

ሕጻናትን ማሠራት የተከለከለ መሆኑ በሕጉች ቢደነገግም፣ በከተማና በገጠር ሕጻናትን ማሠራት አሳሳቢ ችግር ሆኗል። በሕጉ መሠረት በሠራተኝነት ለመቀጠር ዝቅተኛው ዕድሜ 14 ዓመት ሲሆን፣ ይህም ከአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የመጨረሻ ዕድሜ ጋር የሚጣጣም ነው። ዕድሜአቸው ከ14 እስከ 18 ዓመት የሆኑት ልጆች እጅግ

አድካሚ ወይም የሌሊት ሥራ እንዳይሠሩ በልዩ ድንጋጌዎች ተሸፍኗል። እንደዚሁም ዕድሜአቸው ከ14 እስከ 18 ዓመት የሆናቸው ልጆች ከሰባት ሰዓት የበለጠ እንዳይሠሩ፣ ከምሽቱ አራት ሰዓት እስከ ጧቱ 12 ሰዓት ምንም ዓይነት ሥራ እንዳይሠሩ፣ በሕዝባዊ በዓላት ወቅት እንዳይሠሩና የትርፍ ሰዓት ሥራ መሥራት እንደሌለባቸው በሕግ ተደንግጓል። መንግሥት በፋብሪካዎች ውስጥ መሥራትን ፣ ወይም ተንቀሳቃሽ አካላት ባላቸው የማምረቻ ዕቃዎች ላይ መሥራትን፣ ወይም የልጆችን ጤና በሚያውኩ ሥራዎች ላይ መሥራትን እንደ አድካሚ ሥራ በመውሰድ የሕግ ትርጉም ሰጥቶታል።

ሕጻናት ከመሥራት እንዲጠበቁ የሚደነግጉ ሕጐችን የማስፈጸም ኃላፊነት በሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒሰቴር ላይ ተጥሏል። መንግሥት እነዚህን ሕጐች በግልጽ በሚንቀሳቀሰው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ተግባራዊ ለማድረግ አንዳንድ ጥረት ቢያደርግም፤ በበጐ አድራጐት ድርጅቶች፣ ሲቪል ማሕበራት፣ የመንግሥት ሹማምንት እና ቀጣሪዎች እምነት ሕጻናትን ማሠራት፣ በተለይ በግብርና በሚተዳደረው ገጠርና በውል ባልታወቁ አነስተኛ የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴዎች በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በስፋት የሚታይ ችግር ነው። በከተሞች ደግሞ በርካታ ሕጻናት ጫማ በመጥረግ፣ በልብስ ስፌት፣ "በወያላነት"፣ በተሽካሚነት፣ የሎተሪ ቲኬት፣ እና ሌሎች ጥቃቅን ዕቃዎችን በመሸጥ፣ እና በመሳሰሉት ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። በገጠር ደግሞ ሕጻናት በቤተሰብ እና በንግድ እርሻዎች፤ እንዲሁም በቤት ወስጥ ሠራተኛነት ያገለግላሉ።

የዓለም የሠራተኛ ድርጅት በ1993 ዓ.ም. ያካሄደው ሕጻናትን ከማሠራት የመጠበቅ ጥናት በየካቲት 1995 ዓ.ም. ላይ በሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒሰቴር ይፋ ሆኗል። በጥናቱ መሠረት 40% የሚሆኑት ሕጻናት ስድስት ዓመት ሰይሞላቸው ሥራ ይጀምራሉ። ዕድሜአቸው ከ5 እስከ 17 የሆኑ ሕጻናት በአንድ በጥናቱ በተካተተ ሳምንት ውስጥ በሥራ ላይ ያዋሉት አማካይ ሰዓት 32.8 ነበር፣ ዕድሜአቸው ከ5 እስከ 9 ዓመት ከሆናቸው ልጆችና ልጃገረዶች ውስጥ 13% ያህል የሚሆኑት በሳምንት ከ58 እስከ 74 ሰዓት ሠርተዋል። በጥናቱ ከተካተቱት አጠቃላይ ሕጻናት ውስጥ ሁለት ሶስተኛ የሚሆኑት ሁሉንም ወይም የተወሰነውን ገቢያቸውን ለወላጆቻቸው ወይም ለአሳዳጊዎቻቸው ይሰጣሉ። በበቂ አዝመራ አለመሰብሰብ ምክንያት የቤተሰቡ ገቢ መቀነስ እና ትምህርታቸውን አቋርጠው ሥራ የፈቱ ልጆች ለሕጻናት በሥራ መሰማራት አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የሚሠሩ ሕጻናት በአብዛኛው ተንገላተዋል። በ1991 ዓ.ም. የተደረገ ጥናት እንዳረጋገጠው የሚሠሩ ሕጻናት ከማይሠሩት ጋር ሲነጻጸሩ የአካልና የአእምሮ ጉዳት የደረሰባቸው በሁለት እጥፍ፣ መደፈር በአምስት እጥፍ፣ እና መገለል ደግሞ በስምንት እጥፍ ሆኗል። ጥናቱ ካካተታቸው የሚሠሩ ሕጻናት ውስጥ አስገድዶ መድፈር የተፈጸመባቸው ሁሉም በቤት ሠራተኛነት ያገለግሉ ነበር።

መንግሥት በጣም አሰቃቂ የሕጻናት ሥራ በሚል ካስቀመጣቸው ውስጥ ዝሙት አዳሪነትና እንደባሪያ አስሮ ማሠራት ነበሩ። በዓመቱ ውስጥ በቀረቡት ዘገባዎች መሠረት አስገድዶ ወይም እንደ ባሪያ አስሮ ማሠራት የተከሰተው በቤት ሠራተኝነት እንዲያገለግሉ ከደቡብና ከኦሮሚያ ክልሎች ወደሌሎቹ ክልሎች የተጋዙ ይገኙበታል (ክፍል 5 ይመልከቱ)። ወጣት ልጃገረዶች በቤተሰብ አባላት ተገደው ወደሴትኛ አዳሪነት መግባታቸው ተዘግቧል (ክፍል 5 ይመልከቱ)።

ሠ/ ተቀባይነትን ያገኙ የሥራ ሁኔታዎች

በግልና በመንግሥት ተቋማት ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች ዝቅተኛ ደሞዝ $14 (ብር 120) እንዲሆን በሕግ ተደንግጓል። በተጨማሪም እያንዳንዱ ኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፍ የየራሱን ዝቅተኛ ደመወዝ ወስኗል። ለምሳሌ ደሞዝ ከሚያገኙት መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የመንግሥት ሠራተኞች በወር $20 (ብር 175) ያህል ዝቅተኛ ደሞዝ ሲያገኙ፣ በባንክና ኢንሹራንስ ዘርፍ የተቀጠሩ ሠራተኞች ደግሞ በወር $23 (ብር 200) ዝቅተኛ ደሞዝ አግኝተዋል። የደሞዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች አጥኚ ጽ/ቤት እንደገለጸው እነዚህ ክፍያዎች ለሠራተኛውና ለቤተሰቡ መጠነኛ የተደላደለ ኑሮ የሚበቁ አልሆኑም። ስለዚህ፣ አብዛኛዎቹ ቤተሰቦች በሕይወት ለመቆየት ቢያንስ ሁለት አባላቱ መሥራት ስለሚኖርባቸው፣ ሕጻናት ትምህርታቸውን ማቋረጥ ተገድደዋል። በተመጨሪም ደሞዝ የሚያገኘው ሠራተኛ በቁጥር አነስተኛ እና በከተሞች የተከማቸ ነበር።

በሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42 መሠረት፣ አንድ ሠራተኛ በቀን 8 ሰዓት እየሠራ ስድስት ቀናትን በያዘ መደበኛ ሳምንት 48 ሰዓት መሥራትና የ24 ሰዓት እረፍት ማግኘት ይገባዋል። በተግባር ግን ብዙዎቹ በቀን ለ8 ሰዓት እየሠሩ 5 ቀናትን በያዘ የሥራ ሳምንት ለ40 ሰዓት አገልግሎት ሰጥተዋል።

መንግሥት፣ አሠሪዎችና የሠራተኛ ማኅበራት የጤናና የጥንቃቄ ደረጃዎችን ለመወሰን ቢደራደሩም፣ በበቂ የገንዘብና የሰው ኃይል እጥረት የተነሳ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ኢንስፔክሽን መምሪያ በሚገባ ተግባራዊ ሳያደርጋቸው ቀርቷል። ዝርዝር የየኢንዱስትሪው የጤና እና የጥንቃቄ ደንቦች አለመኖር ለተግባራዊነቱ ውስንነት አስተዋጽኦ አድርገዋል። ሠራተኞች የመሥራት ዕድላቸውን ሳያጡ ራሳቸውን ከአደገኛ የሥራ አካባቢዎች የማግለል መብት ቢኖራቸውም፣ ከሥራ እንባረራለን በሚል ፍርሃት ተግባራዊ አላደረጉትም።

የአገሪቱ የሠራተኛ ሕጐች ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩ ሕጋዊ የውጭ አገሮች ሠራተኞችን መብትም ይጠብቃሉ።